# የመሬት ልማትና አስተዳደር ቢሮ ስልጣንና ተግባር አዋጅ 74/2014

1 _የመሬት ልማትና አስተዳደር ቢሮ በአዋጅ የሚከተሉት ስልጣንና ተግባራት ይኖሩታል፡- የመሬት ልማትና አስተዳደር ቢሮ ስልጣን፣ ተግባርና ኃላፊነት

1. የከተማ መዋቅራዊ ፕላን እና ዝርዝር የአካባቢ ልማት ፕላኖች መሰረት በማድረግና ፍትሃዊና ኢኮኖሚያዊ የመሬት ልማትና አቅርቦት እንዲሁም የከተማ ማደስ ጥናት ስራዎችን ያከናውናል፤ እንዲከናወን ያደርጋል፤ አፈጻጸሙን ይከታተላል፤

2. የልማት ቅደም ተከተል በማውጣት የመልሶ ማልማት ፕሮጀክት ጥናት፣ መርሀ ግብሮች፣ ጥቅል ዓላማዎች፣ ግቦች፣ የኢንቨስትመንት ዕቅዶች፣ በጀት፣ የዓላማ ማስፈፀሚያ ስትራቴጂዎችና የጊዜ ሠሌዳ ያዘጋጃል፤ ሲጸድቅ ተግባራዊ ያደርጋል፤

3. ለመልሶ ማልማትና ለመሬት ዝግጅት ተፈላጊው መሰረተ ልማት እንዲጠና ለሚመለከታቸው አካላት ያሳውቃል፤ መጠናቱን ያረጋግጣል፤ ከገንቢዎች በሚገኝ ግብዓት የግንባታ ቅንጅት እቅድና በጀት ያዘጋጃል፤ ሲፈቀድም ያስገነባል፤

4. የመሬት አቅርቦትና ፍላጎት ሚዛኑን ጠብቆ መሄድ እንዲችል የተለያዩ ጥናቶችን በማከናወን የውሳኔ ሃሳብ አዘጋጅቶ ለሚመለከተው አካል ያቀርባል፤ ሲጸድቅም ተግባራዊ ያደርጋል፤

5. በከተማ ማዕከላትና ኮሪደሮች በአካባቢ ልማት ፕላን መሰረት የተቀናጀ የከተማ ንድፍ ያዘጋጃል/እንዲዘጋጅ ያደርጋል፤ በሚመለከተው አካል ሲጸድቅ ተግባራዊ ያደርጋል፤

6. ለተለያዩ ማህበራዊና ኢኮኖሚያዊ አገልግሎቶች የሚውል መሬት ወሰን ያስከብራል፤ አዘጋጅቶ ያቀርባል፤

7. በከተማው ውስጥ የተጎዱና ያረጁ አካባቢዎችን ለማደስ እንዲቻል የካሳ ክፍያ ስርዓት ጥናት ከሚመለከታቸው አካላት ጋር በመተባበር ያከናውናል፤ በየጊዜውም እንዲሻሻል ያደርጋል፤ የነዋሪዎቹን ተጠቃሚነት ባረጋገጠ ሁኔታ ስታንዳርዱን ጠብቆ መልሶ ማልማት የሚያስችል ስርዓት ይዘረጋል፤

8. ለግንባታ ተረፈ ምርት መድፊያነት አገልግሎት የሚሰጡ ቦታዎችን አስመልክቶ የአሰራር ስርዓት ይዘረጋል፤ ይከታተላል፤ ይቆጣጠራል፤

9. የልማት ተነሺዎች የምትክ ቤት ፍላጎት ያጠናል፤ የምትክ ቤት መቀበያ ሰርተፊኬት ይሰጣል፤ ለሚመለከተው አካል ያሳውቃል፤ ሲፈቀድም ለተነሽዎች ምትክ ቤት ድልድል በማድረግ እንዲሰጣቸው ለቤቶች ኮርፖሬሽን ያስተላልፋል፤ የተሰጣቸው መሆኑን ያረጋግጣል፤

10. ለልዩ ልዩ የልማት ስራዎች የለማ መሬት፣ በይዞታነት ለማንም አካል ያልተላለፉ የተዘጋጁና ያልተዘጋጁ ቦታዎችን፣ ባንክ የተደረጉ ክፍት መሬቶችን ወይም ይዞታዎችን ይመዘግባል፤ በዲጂታል እና በፕላን ፎርማት ተገቢውን መረጃ ይይዛል፤ የቦታውንም አገልግሎት ደረጃ እና አስፈላጊ መግለጫዎችን የያዘ የመለያ ሰሌዳ ይተክላል፤ የቦታዎቹን ዝርዝር መረጃ ለደንብ ማስከበር ኤጀንሲ ያስተላለፋል፤ ከኤጀንሲው ጋር በመተባበር ለሕገወጥነት እንዳይጋለጡ ያደርጋል፤

11. በከተማው አስተዳደር ወሰን ክልል ውስጥ ያለውን የመሬት ሃብት ኦዲት ያደርጋል፤ በኦዲት ግኝቱ መሠረት ህጋዊ እርምጃ ይወስዳል ወይም እንዲወሰድ ያደርጋል፤

12. የይዞታ እና የማይንቀሳቀስ ንብረት በመመዝገብ ለመሬት ይዞታ ምዝገባና መረጃ ኤጀንሲ እስኪተላለፍ ድረስ ጥበቃ ያደርጋል፤ የቦታ ይዞታ ማረጋገጫ የምስክር ወረቀት ይሰጣል፤

13. በካርታ በተደገፈ መልኩ የከተማ ቦታ ደረጃ፣ የሊዝ መነሻ ዋጋ እና አማካይ የሊዝ ዋጋ ጥናት ያካሂዳል፤ ወቅታዊ እንዲሆኑ ያደርጋል፤ ሲጸድቅም ተግባራዊ ያደርጋል፤

14. በከተማ ክልል ወስጥ ለልዩ ልዩ የልማት ሥራዎች የለማ መሬትን በመመዝገብ ወጥ የሽንሻኖ ቁጥር ይሰጣል፤ በጨረታ እና በምደባ የሚተላለፉ ቦታዎችን ይለያል፤ ቦታው ለተጠቃሚ እስከሚተላለፍ ድረስ ከደንብ ማስከበር ኤጀንሲ ጋር በመቀናጀት የመከላከልና የመጠበቅ ሥራ ያከናውናል፤

15. መሠረተ ልማት ተሟልቶላቸው የተዘጋጁ የከተማ ቦታዎች ለአልሚዎች የሚተላለፉበትን ሥርዓት ይዘረጋል፤ አግባብ ባለው ህግ መሠረት መሬት ለባለሙብት ያስተላልፋል፤ ቦታውን በመስክ ያስረክባል፤ በሊዝ ህግና ዉል መሠረት የሊዝ ክፍያ ይሰበስባል፤

16. አግባብ ባለው ህግና የሊዝ ውል መሠረት ግንባታ መከናወኑን ያረጋግጣል፤ በሕግና በውል በተወሰነው ጊዜና ሁኔታ መሬቱ መልማቱን ያረጋግጣል፤ የሊዝ ውል ማሻሻያ ያደርጋል፣ መሬቱ ካለማ ህጋዊ እርምጃ ይወስዳል፤ እንዲወሰድ ያደርጋል፤

17. ለጊዜያዊ መጠቀሚያነት አገልገሎት የሚሰጡ ቦታዎችን በጊዜያዊ የሊዝ ውል ያስተላልፋል፤ የውል ጊዜያቸው ወይም አገልግሎታቸው ሲያበቃ ቦታውን በመረከብ ለዳግም ልማት ያዘጋጃል፤

18. ለልማት ይዞታቸውን የሚለቁ ባለይዞታዎች ከመልቀቃቸው በፊት አግባብ ባለው ህግ መሰረት የይዞታ ማስለቀቅ ሂደቱን ይተገብራል፤ የተነሽ አርሶ አደሮችን ዝርዝር እና መረጃ ለአርሶ አደርና ከተማ ግብርና ልማት ኮሚሽን ያስተላልፋል፤

19. የልማት ተነሺዎች ይዞታቸውን ከመልቀቃቸው በፊት አግባብ ባለው ሕግ መሠረት የምትክ ቦታ፣ ቤት፣ ተመጣጣኝ የንብረት ካሳ እና ሌሎች ክፍያዎች የሚያኙበትን ሥርዓት ይዘረጋል፤ ለልማት በሚለቀቀው መሬት ላይ ላለው ንብረት በህግ መሠረት ካሳ ይተምናል፤ እንዲተመን ያደርጋል፤ የንብረት ካሳና ሌሎች ክፍያዎችን ይፈጽማል፤ ምትክ ቦታ ያዘጋጃል፤ ምትክ ቦታ ያስተላልፋል፤

20. ለመሠረተ ልማት አውታር፤ ለመናፈሻ፣ ለአረንጓዴ ልማት እና ለሕዝብ መሰብሰቢያ ፕላዛዎች በመዋቅራዊ ፕላኑ መሠረት ቦታ ያዘጋጃል፤ ያስተላልፋል፤ የይዞታ ማረጋገጫ የምስክር ወረቀት ይሰጣል፤

21. ለልዩ ልዩ የግንባታ ስራዎች ሊያገለግሉ የሚችሉ የማዕድን ማውጫ ቦታዎች በመዋቅራዊ ፕላኑ መሠረት ከልሎ ይይዛል፤ በአካባቢ ጥበቃ ባለስልጣን በተሰጠ የማዕድን ማዉጫ ፈቃድ መሠረት በጊዜያዊ የሊዝ ውል መሬቱን ያስተላልፋል፤ የማእድን ማውጣት ሥራው ሲጠናቀቅ ወይም ፈቃዱ ሲሰረዝ ወይም የሊዝ ውሉ ጊዜ ሲያበቃ መሬቱን በመረከብ ለዳግም ልማት ያዘጋጃል፤

22. የመሬት ይዞታ እና የቤት አጠቃቀም ዓይነትና የባለይዞታዎች መረጃ ይይዛል፤ ይጠብቃል፤ አግባብ ባለው ህግ መሠረት ለህጋዊ ባለይዞታዎች የቦታ አገልግሎት ለውጥ ጥያቄዎች መርምሮ ውሳኔ ይሰጣል፤

23. አግባብ ባለው ህግ መሠረት የቤት/ህንጻ የጣራና ግድግዳ ግብር ተመን ያሰላል /እንዲሰላ ያደርጋል ለሚመለከተው አካል በወቅቱ ያስተላልፋል፤

24. ለግብር ሰብሳቢ ተቋማት፣ ለፍርድ ቤቶችና ለሌሎች ለሚመለከታቸው አካላት የማይንቀሳቀስ ንብረት ግምት አገልግሎት ይሰጣል፤

25. መደበኛ የይዞታ አገልግሎቶችን ያከናውናል፤ ህጋዊ ያልሆነ የይዞታ አስተዳደር አፈፃፀም ሲከሰት የማስተካከያ እርምጃ ይወስዳል፡፡

26. በህግ የሚቀመጠውን የአሰራር ስርአት ተከትሎ መብት ላልተፈጠረላቸው ይዞታዎች የይዞታ ማረጋገጫ ምስክር ወረቀት በማዘጋጀት በቋሚ መዝገብ በመመዝገብ ለባለይዞታው ይሰጣል፤ ማህደራቸውን ያደራጃል፤ ከሕግ ውጪ የተሰጠ የቦታ ይዞታ ወይም የቤት ባለቤትነት የይዞታ ማረጋገጫ የምስክር ወረቀት አግባብ ባለው ሕግ መሰረት ያግዳል፣ እንደአስፈላጊነቱ ይሰርዛል/ያመክናል/፤

27. የቦታ ይዞታ እና/ወይም የቤት ይዞታ ካርታ ኮፒዎችን በወቅቱ ለሚመለከተው አካል ያስተላልፋል፤ የይዞታ ሰነዶችን በማደራጀት ለመሬት ይዞታ ምዝገባና መረጃ ኤጀንሲ ያስተላልፋል

28. ለሕዝብ ጥቅም ሲባል የመሬት ይዞታቸውን የለቀቁ ተነሺዎችን መልሰው በዘላቂነት ያቋቁማል፤ ይህን ተግባራዊ ለማድረግ፡-

ሀ) የማቋቋሚያ ማዕቀፍ ይቀርጻል፤ ለከንቲባ ያቀርባል፤ ሲጸድቅ ተግባራዊ ያደርጋል፤

ለ) የልማት ሥራው በሚሰራበት ወቅት ተነሺዎች በተቻለ መጠን የስራ እድል እንዲያገኙ ያደርጋል፤

ሐ) የተነሺዎችን የኢንቨስትመንት ሼር ባለቤትነት መብት ያስከብራል፤ ተጠቃሚ መሆናቸውን ይከታተላል፤ ይደግፋል፤

መ) የልማት ተነሺዎች የኢንቨስትመንት ባለቤት የሚሆኑበትን የአሰራር ሥርዓት ይዘረጋል፤

ሠ) ሌሎች አግባብ ባላቸው ሕግ ደንብና መመሪያ የተገለጹትን ተግባራትና ኃላፊነቶች ይፈጽማል፡፡

29. በየደረጃው ያለውን የቢሮ ዘርፎችን፣ ዳይሬክቶሬቶችን ፣የቅርንጫፍ ጽ/ቤት አመራር እና ባለሙያዎችን ህግና አሰራርን ተከትሎ ያሾማል/ይመድባል፣ አስፈላጊ ሆኖ ሲገኝ ተገቢውን እርምጃ ይወስዳል /ያስወስዳል፣

**የቢሮው ራዕይ፣ ተልዕኮ እና ዕሴቶች**

**የመሬት ልማትና አስተዳደር ቢሮ ራዕይ /Vision/**

በ2022 ዓ.ም ዘመናዊ የመሬት ልማትና አስተዳደር ስርዓት የተዘረጋበት፤የላቀ አገልግሎት የሚሰጥበት እና የተገልጋይ እርካታ የተረጋገጠበት ተቋም ሆኖ ማየት

**የመሬት ልማትና አስተዳደር ቢሮ ተልዕኮ /Mission/**

በአዲስ አበባ ከተማ አሰራርን የተከተለ እና ውስን የሆነውን የመሬት ሀብት ያማከለ የመሬት ዝግጅትና ማስተላለፍ ስራ ማከናወን፤ የተጎሳቆሉ አካባቢዎችን መልሶ በማልማት፤ የተቀናጀ የመሬት መረጃ አያያዝ እና የመሬት ባንክ ስርዓት በመዘርጋት የመብት ፈጠራ ስራን በማከናወን ፍትሃዊ ቀልጣፋ እና ውጤታማ አገልግሎት መስጠት፡፡

**የመሬት ልማትና አስተዳደር ቢሮ እሴቶች /Values/**

- አሳታፊነት፣
- ግልፅነት
- ፍትሀዊነት
- የላቀ አገልግሎት መስጠት
- በኃላፊነት ስሜት መስራት
- ተጠያቂነት

**የቢሮው ባለድርሻ አካላት**

- የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የመንግስት መስሪያ ቤቶች
- የፌዴራል መንግስት ተቋማት፤ የሃይማኖት ተቋማት
- የመሰረተ ልማት ዘርፍ ተቋማት፤ ማህበራት
- የፋይናንስ ተቋማት፤ አርሶ አደሮች
- የስነ ምግባርና ፀረ ሙስና ኮምሽን
- ብርሃን እና ሰላም ማተሚያ ድርጅት

**የመሬት ልማትና አስተዳደር ቢሮ የደንበኞች መብትና ግዴታዎች**

**የደንበኞች መብቶች**

- አካል ጉዳተኞች፤ በእድሜ የገፋ አረጋውያንና ልዩ ትኩረት የሚሹ የህዝብ ክፍሎች በልዩ ትኩረት መስተንግዶና አገልግሎት ማግኘት፤
- በቂና ወቅታዊ ምላሽ ባጡበት ጊዜ ለሚመለከታቸው የስራ ኃላፊዎች፤ ለሚዲያ፤ ለህዝብ እምባ ጠባቂ፤ ለሰብአዊ መብት ኮሚሽንና፤ ለሌሎች የሚመለከታቸው አካላት ማሳወቅ፤
- ስለአገልግሎቱ ሙሉ መረጃ የማግኘትና የመጠቀምና የሚጠይቀውን ወጪ የማወቅ መብት፤
- አገልግሎቱን ለማግኘት ተጨማሪ መረጃ ካስፈለገ ማግኘትና ጉዳዩን በትህትና ማስረዳት፤ በተቋሙ የማመልከቻ ቅፁን በትክክል መሙላትና ተጨማሪ ጉዳይ ሲኖር በፅሁፍ መጠየቅ፤
- ግልፅና ተጠያቂነት ያለበትና ከአድሎ የፀዳና ፍትሃዊ አገልግሎት በስታንዳርዱ መሠረት የማግኘት መብት፤
- ወቅታዊ፣ ፍትኃዊ እና ህግና ሥርዓትን የተከተለ ሙያዊ ምላሽ የማግኘት መብት፤
- በክብር መስተናገድ፤ የመመካከር መብት፤
- ተገቢውን አገልግሎት ካላገኙ ለሚመለከተው አካል የማሳወቅና ተገቢውን አገልግሎት ለማግኘት የመጠየቅ መብት፤
- በተጨባጭ መረጃ/ማስረጃ የተደገፈ ቅሬታና አስተያየት የማቅረብ፤ላቀረቡት ቅሬታም ተገቢውን ምላሽ በሰዓቱ የማግኘት መብት፤

**የደንበኞች ግዴታ**

- ለጥበቃ ሀይል መታወቂያ በመስጠት እና ሲገቡ ለፍተሻ መተባበር
- የባለጉዳይ መስተንግዶ ባጅ በመውሰድ አንገት ላይ በማንጠልጠል እና ጉዳዩን ሲጨርሱ ባጁን በመመለስ መታወቂያውን መውሰድ፤
- ወደ ቢሮው ሲመጡ መታወቂያ ይዞ መምጣት፤
- ተገልጋዮች አገልግሎቱን በሙሉ ወይም በከፊል ለማግኘት ሲመጡ ማሟላት ያለባቸውን ቅድመ ሁኔታዎች ማሟላት አለባቸው።

**የመሬት ልማትና አስተዳደር ቢሮ መብት እና ግዴታ**

**የመሬት ልማትና አስተዳደር ቢሮ መብት**

- በሀገሪቱ ውስጥ ባሉ የህግ ማዕቀፎችን መሰረት ያደረገ አገልግሎት መስጠት
- በከተማ አስተዳደሩ ባሉ የህግ ማዕቀፎችን መሰረት ያደረገ አገልግሎት መስጠት

**የመሬት ልማትና አስተዳደር ቢሮ ግዴታ**

- የተቋሙን ሰራተኞችና ተገልጋዮች ማሳተፍ፣
- የዜጎች ቻርተር በቀጣይነት የሚሻሻል መሆኑን ግምት ውስጥ ማስገባት፣
- ቀላልና ሊታይ የሚችል ማሻሻያ በመውሰድ ተገልጋዮች በተቋሙ ላይ እምነት እንዲያሳድሩ ማድረግ፣
- የተገባውን ቃል ለተገልጋይ በግልፅ ማሳወቅ፣
- በቻርተር ትግበራ ሂደት ከሰራተኞች የሚጠበቀውን ሀላፊነትና ሚና በስልጠና ማጎልበት
- ሰራተኞች ኃላፊነታቸውን በትክክል እንዲወጡ የመወሰን ስልጣን መስጠት፣
- በገለልተኛ አካል በመገምገም ግብረ መልስ ለማግኘት የሚያስችል ስርዓት መዘርጋት፣

**ለተገልጋዮች የምንገባው ቃል**

- ተገልጋዮቻችን በዚህ  መሠረት በፍትሃዊነትና ያለአድልዎ የሚጠየቁ አገልግሎቶችን እንሰጣለን፤
- ተገልጋዮቻችን የሚፈልጉትን አገልግሎት በክብር፤ እንሰጣለን፤

| ተ/ቁ | የሚሰጡ ዋና እና ንዑስ አገልግሎቶች ዓይነት | የሚሰጥበት የአስተዳደር እርከን የ✓ ያድርጉ | | | |
|---|---|---|---|---|---|
| | | በማዕከል | በክ/ከተማ | በወረዳ | ምርመራ |
| | **ዋና እና ንዑስ/ዝርዝር አገልግሎቶች** | | | | |
| 1. | የለማ መሬትን ለአልሚዎች ማስተላለፍ እና ሊዝ ማዋዋል | ✓ | | | |
| | - በታዎችን በሊዝ ጨረታ ማስተላለፍ፣ | ✓ | | | |
| | - በታዎችን በምደባ ማስተላለፍ፣ | ✓ | | | |
| | - በጊዜያዊ መጠቀሚያ በታን በሊዝ መፍቀድ | ✓ | | | |
| | - በሊዝ የተላለፉ በታዎችን አገልግሎት ለውጥ መፍቀድ | ✓ | | | |
| | - የሊዝና የክፍያ ገቢ ማሰብሰብ | ✓ | ✓ | | |
| 2. | - የመልሶ ማልማትና ወሰን ማስከበር | | | | |
| | - የልማት ተነሺዎችን ቅድሚያ የማልማት ጥያቄዎችን ተቀብሎ አገልግሎት ማስጠት | ✓ | ✓ | | |
| 3. | ከህግ እና ቴክኒክ ጉዳዮች ከተገልጋዮ የሚቀርቡ ቅሬታዎች መቀበልና ምላሽ ማስጠት፣ | | | | |
| | - ከፍ/ቤት የሚቀርቡ ጉዳዮችን መቀበለና ምላሽ ማስጠት | ✓ | ✓ | ✓ | |
| | - የፍ/ቤት እግድ መቀበልና ሚፈፀም | ✓ | ✓ | ✓ | |
| 4. | - የልማት ተነሺዎችን መልሶ ማቋቋም አገልግሎት | ✓ | | | |
| | - በሽርክና ለማልማት ፍላጎት ያላቸውን ማለየትእና ማስተናገድ | ✓ | | | |
| 5. | የመሬት ፈጠራ ስራዎችን ማስራት | | | | |
| | የመስክ ልኬት ቅየሳ ስራ የካርታ ህትመት አገልግሎት ማስጠት | ✓ | | | |
| | ለሚቀርቡ አቤቱታዎች አጣርቶ ምላሽ ማስጠት | ✓ | | | |
| | የጂ አይ ኤስ እና የሲ አይ ኤስ ሚረጃ እርማት ማድረግ | | | | |
| | የይካከተትልኝ ጥያቄ ማስተናገድ | ✓ | | | |
| | የይዞታ አገልግሎቶችን ማስጠት፣ | ✓ | ✓ | | |
| 6. | የይዞታ አገልግሎት ለውጥ ማፅደቅ | ✓ | | | |
| | በይዞታ ይገባኛል ክርክር ለፍርድ ቤት ማስረጃ ማስጠት | ✓ | ✓ | | |
| | - ይዞታ መቀላቀል አገልግሎት ማስጠት ( ለነባር ብቻ ) | | ✓ | ✓ | |
| | - የባለይዞታነት ወይም የቤት ባለቤትነት ወይም የወሰን ክርክር መፍታት | ✓ | ✓ | | |
| 7. | የበታ ማስረከብና የሊዝ ክትትል | | ✓ | | |
| - | - የለማ መሬት በጨረታ ማስተላለፍ | ✓ | | | |

| | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|
| 8. | – የለማ መሬት በምደባ ማስተላለፍ | | | | |
| | – የጊዜያዊ መጠቀሚያ ቦታዎች ማስተላለፍ | ✓ | | | |
| | – ለልማት ተነሽዎች ምትክ ቦታ ማስተላለፍ | ✓ | ✓ | | |
| 9. | የሊዝ ውል ማዋዋል | ✓ | | | |
| | – የሊዝ ውል ማሻሻያ ማድረግ | ✓ | | | |
| | – የሊዝ መብት ማስተላለፍ | ✓ | ✓ | | |
| | – የለማ መሬት አዘጋጅቶ ለአልሚዎች ማቅረብ | ✓ | | | |
| | – የመስክ የቅየሳ ስራ ማሰራት (ተገለጋዩ ባለበት) | ✓ | | | |
| 10. | የቦታ ሽናሻኖ ስራ ማሰራት (ተገለጋዩ ባለበት) | ✓ | | | |
| | – የልማት ተነሽዎች መረጃ አሰባሰብ | ✓ | | | |
| | – የልማት ተነሽዎች መረጃ አገናዝቦ መቀበል | ✓ | ✓ | | |
| | – የመስክ ልኬት መረጃዎች በመውሰድ የይዞታ ማረጋገጫካርታ መስጠት | ✓ | | | |
| | – በተለያዩ የቅየሳ መሳርያዎች የመስክ ልኬት መረጃዎች መውሰድ፣ | ✓ | ✓ | | |
| | – በተሰበሰበው የቴክኒክ መረጃ ላይ በመስክ ልኬት የተገኙ አካላትን ማስፈረም | ✓ | ✓ | | |
| | – **ከፍትህ እና ሌሎች አካላት ለሚጠየቁ ጥያቄዎች ተገቢ ምላሽ /ማስረጃ/ መስጠት** | | | | |
| 11. | አገልግሎት ጥያቄ መቀበል እና ማህደር ማውጣት | | ✓ | | |
| | – በመስክ መረጃ መውሰድ የሚያስፈልገው ከሆነ በተለያዩ የቅየሳ መሳርያዎች የመስክ ልኬት መረጃዎች መውሰድ፣ | ✓ | ✓ | | |
| | – መረጃዎችን አደራጅቶ ምላሽ መስጠት | ✓ | ✓ | | |
| | – **የይዞታ አገልግሎት መስጠት** | ✓ | ✓ | | |
| 12. | በሚቀርቡ ቅሬታዎች መቀበል | | ✓ | | |
| | – የተለዩ ክፍተቶችን ማጣራትና መመርመር | ✓ | ✓ | | |
| | – የካርታ ኮፒ አገልግሎት መስጠት | ✓ | ✓ | | |
| | – የባለቤትነት ስመ ንብረት ዝውውር አገልግሎት መስጠት | | ✓ | | |
| | – ይዞታ መክፈል አገልግሎት መስጠት | | ✓ | | |
| | – ይዞታ መቀላቀል አገልግሎት መስጠት | የነባር ብቻ | ✓ | | |
| | – የቤት አገልግሎት ለውጥ መፍቀድ | ✓ | ✓ | | |
| | – ለመኖሪያ ቤት ህብረት ስራ ማህበራት፣ ለኮንዶሚኒየም ለሪል ስቴት የተናጠል ካርታ መስጠት፤ | ✓ | ✓ | | |
| | – ለሚቀርቡ ቅሬታዎችን ምላሽ መስጠት | | ✓ | ✓ | |
| | – **ለህጋዊ ይዞታዎች የሰነድ ማረጋገጥ መስጠት** | ✓ | ✓ | | |

| | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|
| 13. | የዋስትና እዳ እገዳ ምዝገባ አገልግሎት | | ✓ | | |
| . | የዋስትና እና እዳ እገዳ ስረዛ አገልግሎት | | ✓ | | |
| 16. | ከፍትህ እና ከሌሎች አካላት ለሚጠየቁ ጥያቄዎች ተገቢ ምላሽ /መረጃ/ መስጠት፣ | | ✓ | ✓ | |
| 17. | ውሰን ማሳወቅ እና የውሰን ድንጋይ መትከል | ✓ | ✓ | | |
| 18 | ለግብር ሰብሳቢ ተቋማት፣ ለፍርድ ቤቶችና ለሌሎች ለሚመለከታቸው አካላት የቤት/ህንጻ ግምት አገልግሎት መስጠት፤ | | ✓ | ✓ | |
| 21 | ከሚመለከታቸው አካላት ለሚቀርቡ ጥያቄዎች ምላሽ መስጠት | | ✓ | ✓ | |
| 22 | ከ1988 እስከ ግንቦት 1997 የተያዙ ይዞታዎችን መረጃ ከአመልካቾች መረከብና መሀደር ማደራጀት | ✓ | ✓ | ✓ | |
| 23 | የይዞታዎች ከ1997 ዓ.ም በፊት የተያዙ ስለመሆናቸው ከ1997ቱ የአየር ካርታ፣ በአካልና በሰነድ ማረጋገጥ | | ✓ | ✓ | |
| 24 | የአርሶ አደርና የአርሶ አደር ልጆች ሜዳ በመሆኑ ማረጋገጥ ማስቀመጥ ሰነድ የሚያገኙበትን አግባብ በሰነድና በአካል የሚረጋገጥአገልግሎት መስጠት | | ✓ | | |
| 25 | የቦታ ኪራይና የቤት ግብር ተመን አስልቶ ለሚመለከተው አካል በወቅቱ ማስተላለፍ | | ✓ | ✓ | |
| 26 | ከፍትህ እና ከሌሎች አካላት ለሚቀርቡ ጥያቄዎች ተገቢ ምላሽ /መረጃ/ መስጠት | | ✓ | ✓ | |

## በቴክኖሎጂ የሚሰጡ አገልግሎቶች

01. በምትክ፣ በጨረታና በምደባ ለሚተላለፉ ቦታዎች አዲስ የይዞታ ማረጋገጫ ካርታ መስጠት አገልግሎት

02. የመኖሪያ ቤት ህብረት ስራ ማህበራት የተናጠል አዲስ የይዞታ ማረጋገጫ ካርታ መስጠት አገልግሎት

03. የኮንዶሚኒየም ቤት ዕጣ/ በጨረታ ለደረሰው ተገልጋይ አዲስ የይዞታ ማረጋገጫ ካርታ መስጠት አገልግሎት

04. የይዞታ ማረጋገጫ ካርታን በአዲስ መልክ አሻሽሎ መስጠት አገልግሎት

05. ቀድሞ በነበረ ህጋዊ ይዞታ ላይ ተጨማሪ ቦታ የማካተት አገልግሎት

06. አስቀድሞ በሕጋዊነት የተሰጠው ካርታ ሲጠፋ/ ስህተት ሲኖረው ምትክ የይዞታ ማረጋገጫ ካርታ መስጠት አገልግሎት

07. የሊዝ የይዞታ ማረጋገጫ ካርታ በማደስ የይዞታ ማረጋገጫ ካርታ መስጠት

08. ሁለት እና ከዚያ በላይ አዋሳኝ የሆኑ በሊዝ-ሊዝ እና በሊዝ-በነባር ስሪት የሚተዳደሩ ይዞታዎችን መቀላቀል አገልግሎት

09. ሁለት እና ከዚያ በላይ አዋሳኝ የሆኑ በነባር ስሪት የሚተዳደሩ ይዞታዎችን መቀላቀል አገልግሎት

10. ለነባር ይዞታ የቤት አገልግሎት ለውጥ በማድረግ የይዞታ ማረጋገጫ ካርታ መስጠት አገልግሎት

11. ለማንኛውም ህጋዊ ይዞታ የይካፈልልኝ አገልግሎት መስጠት

12. በሽያጭ ወይም በስጦታ የስመ ንብረት ዝውውር አገልግሎት

13. በውርስ / በመጋራት የሚተላለፍ የስመ ንብረት ዝውውር አገልግሎት

14. የመኖሪያ ቤት ሕብረት ስራ ማህበራት አባላት መተካካት የስመ ንብረት ዝውውር አገልግሎት

15. የጋራ ሕንጻ/ኮንደሚኒየም የስመ ንብረት ዝውውር አገልግሎት

17. ልዩ ልዩ ይዞታ ነክ ማስረጃዎችን መስጠት አገልግሎት

18. በይዞታ ይገባኛል ክርክር ለፍርድ ቤት ማስረጃ መስጠት አገልግሎት

19. ዋስትናና ዕገዳ የመመዝገብ አገልግሎት

20. ዋስትናና ዕገዳ የመሰረዝ አገልግሎት

21. ለነባር ይዞታዎች የቦታ መጠቀሚያ ኪራይና የቤት ግብር ተመን አገልግሎት

22. የንብረት ግምት አገልግሎት

23. የወሰን ይመላከትልኝ አገልግሎት

24. የደንበኞችን ቅሬታ

25. አግባብ ባለው አካል ሳይፈቀድ ለተያዙ ይዞታዎች የይዞታ ማረጋገጫ ካርታ እስከ ግንቦት 1988 ዓ.ም ድረስ የተያዙ ይዞታዎች የይዞታ ማረጋገጫ ካርታ

27. የአርሶ አደር የመኖሪያ ቤትና የከተማ ግብርና መጠቀሚያ የይዞታ ማረጋገጫ ምስክር ወረቀት መስጠት

.